# מוקד סיוע לעובדים זרים (ע"ר)

"וגר לא תונה ולא תלחצנו כי גרים הייתם בארץ מצרים", שמות כ"ב, פסוק כ'

# እስራኤል ውስጥ ጥገኝነት የሚፈልጉ ሰዎች ስላላቸው መብትና መረጃ የያዘ መጽሔት

<u>በሚከተሉት ድርጅቶች ድጋፍ የተዘጋጀ፦</u>

• የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽነር (United Nations High Commissioner for Refugees) • በቴል አቪብ ዩኒቨርሲቲ የስደተኞች መብት ፕሮግራም (Refugee Right Program at Tel Aviv University) • ለስደተኛ ሠራተኞች የመረጃ ስልክ መስመር • ካቭ ላኦቬድ • የአፍሪካ ስደተኞች እድገት ማዕከል (A.R.D.C. - African Refugees Development Center) • ለስደተኞችና ጥገኝነት ፈላጊዎች የሰነ አእምሮ እርዳታ ድርጅት (A.SS.A.F. - Aid Organization for Refugees and Asylum Seekers) • ለውጭ አገር ሠራተኞች እርዳታና የመረጃ ማዕከል (Mesila - Assistance and Information Center for Foreign Workers) • የሰብዓዊ መብት ዶክተሮች (PHR - Physicians for Human Rights)

ዲሴምበር 2008 ዓ.ም.

## ስደተኛ ሠራተኞች የመረጃ መስመር

"እናንተ በግብጽ ምድር ስደተኞች ነበራችሁና ስደተኛውን አትበድለው፣ ግፍም አታድርግበት።" 22:21

רח' נחלת בנימין 75 ת"א 65154, טל. 03-5602530, פקס. 03-5605175
info@hotline.org.il, www.hotline.org.il

# የተከበሩ ጥገኝነት ፈላጊ፦

እዚህ መጽሔት ውስጥ እስራኤል ውስጥ ሳሉ ጠቃሚ የሆነ መረጃ ያገኛሉ። መብቶችዎን፣ መብቶችዎችን ማስከበሪያ መንገዶችና መብቶችዎን ለማስከበር ሊያጋጥምዎት የሚችሉትን ችግሮች ለመፍታት የሚረዱዎት የድርጅቶች ዝርዝር አካቶ ይዟል።

እስራኤል በ1951 ዓ.ም. የወጣውን ከስደተኞች ሁኔታ ጋር የተያያዘውን ዓለማቀፍ ስምምነት ፈርማና አጽድቃ ቢሆንም፣ ስደተኞች ያላቸውን መብቶች የሚገልጽ ወይም ያላቸውን ሕጋዊ ሁኔታ ደንብ የሚያሲዝ ሕግ አላወጣችም። ሆኖም እስራኤል ውስጥ የተወሰኑ መብቶች አልዎት።

እስራኤል ውስጥ ብዙ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (NGOs) ለጥገኝነት ፈላጊዎች መረጃና አገልግሎቶች ይሰጣሉ። ይህ መጽሔት የያዘው መረጃ የተገኘው ከነዚህ ድርጅቶች፣ ከተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽን እና ከ Mesila ማለትም በቴል አቪብ ከተማ የተቋቋመ የበጎ አድራጎት ድርጅት ነው። እያንዳንዱ ድርጅት የየራሱን መረጃ የሰጠ ሲሆን፣ ለሰጠውም መረጃ ኃላፊነት አለበት።

ይህ መጽሔት የእስራኤል አገርን ኑሮ ሲላመዱ እንደሚረዳዎት ተስፋ እናደርጋለን። የእስራኤል መንግሥት ጥገኝነት ፈላጊዎችን በተመለከተ የሚያወጣው መመሪያዎች ቶሎ ቶሎ ስለሚቀያየሩ፣ የተወሰኑ ችግሮች ሲያጋጥምዎት የሚመለከታቸውን ድርጅቶች እንዲገናኙ እናሳስባለን። እነዚህ ድርጅቶች የተሟላ መረጃ ሊሰጡዎትና ችግሮችዎን እንዴት መፍታት እንደሚችሉ ሊያማክሩዎት ይችላሉ።

ከአክብሮት ጋር

ስደተኛ ሠራተኞች መረጃ መስመር የመስሪያ ቤቱ ሠራተኛ

UNHCR
The UN Refugee Agency

# UNHCR ምንድን ነው?

UNHCR ማለት የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ድርጅት ነው። የድርጅቱ ሚና ለስደተኞች አለማቀፍ ጥበቃ መስጠትና ከስደተኝነት ጋር ለተያያዙ ችግሮች መፍትሔ ማግኘት ነው። UNHCR የ1951 ዓ.ም. ስደተኞች ስምምነት በሥራ ላይ መዋሉንም ይቆጣጠራል። ይህ ስምምነት ስደተኛ ተብሎ የሚጠራው ማን እንደሆነ ፍቺ ይሰጣል፣ እንዲሁም ስደተኞች ስቃይ ሊደርስባቸው የሚችልበት ቦታዎች ጋር እንዳይመለሱ ይከለክላል።

የ UNHCR ቢሮ በእስራኤል የሚገኘው ቴል አቪብ ውስጥ ነው። ይህ ቢሮ የእስራኤል መንግሥት እስራኤል ውስጥ የጥበቃ ማመልከቻዎችን በመመርመር ያግዛል፣ እንዲሁም መንግሥቱ እስራኤል ውስጥ ስደተኛ ነው ብሎ የመመደብ መብት ያለውን ሰው ለመወሰን የሚያስችሉ ግልጽና ትክክለኛ የሆኑ አሠራሮች እንዲያወጣ ያማክራል።

## እስራኤል ውስጥ የጥገኝነትን አሠራር በተመለከተ መረጃ

### ከአገር ከመባረር የሚጠብቅ መብት

የ1951 ዓ.ም. ስደተኞች ስምምነት ጥገኝነት የሚፈልጉ ሰዎች በዘር፣ በሃይማኖት፣ በዜግነት፣ በማህበራዊ አባልነት ወይም በፖለቲካ አስተያየት ምክንያት ለሕይወታቸው ወይም ለነጻነታቸው የሚያሰጋቸው ቦታ እንዳይባረሩ ይከለክላል። ይህ የጸረ-መባረር መመሪያ ማመልከቻ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትሩ የመጨረሻውን ውሳኔ እስከሚያስተላልፍ ድረስ መጠበቅ አለበት።

### የጥበቃ ማመልከቻ ጥያቄ ማስገባት

ጥገኝነት ፈላጊ ሰው እንደ ስደተኛ ጥበቃ የሚፈልግ ሰው ነው። ጥገኝነት ፈላጊዎች ሁሉ ቴል አቪብ የሚገኘው UNHCR ቢሮ ጋር ወይም የአገር ውስጥ ሚኒስቴር መቀበያ ማዕከል ጋር ሄደው በጽሑፍ ማመልከቻ ማስገባት አለባቸው። ይህንን በፋክስ ወይም በፖስታ ማድረግም ይቻላል። ማመልከቻው ከገባ በኋላ፣ እያንዳንዱ አመልካች የምዝገባ ቃለ መጠይቅ ማድረግ አለበት። ጥገኝነት ፈላጊው/ፈላጊዋ እሥር ላይ ከሆነ/ከሆነች፣ ምዝገባው እዛው ይኪያሄዳል። ጥገኝነት ፈላጊው/ፈላጊዋ እስራኤል ሲደርስ/ስትደርስ ታስሮ/

ታስራ ካልነበረ፣ ምዝገባው የሚሆነው ወይ ቴል አቪብ ወይ ሎድ ውስጥ ነው። (ተጨማሪ መረጃ የያዘ ወረቀት ከ UNHCR ማግኘት ይቻላል።)

ጥገኝነት ፈላጊዎች እስራኤል ውስጥ ጥበቃ እንደሚፈልጉና UNHCRን መገናኘት እንደሚፈልጉ ተገቢውን ባለሥልጣኖች ማስታወቃቸው፣ እንዲሁም የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴርን ወይም የስደተኞች ፍርድ ቤት ዳኛንም ጨምሮ ማስታወቃቸው ወሳኝ ነው። ይህን ካደረጉ በኋላ ተገቢዎቹ ባለሥልጣኖች UNHCRን ያስታውቁትና የአመልካቹን ሁኔታ መወሰን የሚያስችለውን ሂደት ይጀምራል።

## የጥያቄው አቀራረብ

የስደተኞች ሁኔታ ውሳኔ (Refugee Status Determination (RSD)) በተባለው አሠራር መሠረት UNHCR ወይም የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር እስራኤል ውስጥ ጥገኝነት ፈላጊዎችን ቃለ መጠይቅ ይሰጣል። ይህ ከላይ ከተጠቀሰው የምዝገባ ቃለ መጠይቅ ረዘም ያለና ዝርዝር ቃለ መጠይቅ ነው። አብዛኛውን ጊዜ ቃለ መጠይቆቹ የሚኪያሄዱት በአስተርጓሚ አማካኝነት በግለሰቡ የትውልድ ቋንቋ ነው። ቃለ መጠይቁ ላይ ጥገኝነት ፈላጊዎች ስለ ግል ሁኔታቸው ዝርዝር ማስረጃ ይሰጣሉ፣ አገራቸውን የለቀቁበትን ምክንያቶችና ቢመለሱ የሚያጋጥማቸውን ችግርም ይናገራሉ።

ጥገኝነት ፈላጊው/ፈላጊዋ ያቀረበው/ያቀረበችው መረጃ፣ ስለ ትውልድ አገሩ/አገሯ ታማኝ መረጃ፣ እንዲሁም ጥገኝነት ፈላጊው/ፈላጊዋ ስላስገባው/ስላስገባችው ጥያቄ ግምገማ አብሮ ሆኖ “The National Status Granting Body” (NSGB) (ብሔራዊ ጉዳይ ኣጽዳቂ ክፍል) ወደታባለው የመንግሥት አማካሪ ኮሚቴ ይተላለፋል። NSGB እያንዳንዱን ጉዳይ በተናጥል ያጤንና የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትሩ ውሳኔ እንዲያስተላልፍ ሓሳቦች ያቀርባል። የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትር ወይም እሱ የሰየመው ሰው አንድ ማመልከቻን የማጽደቅ ወይም የመከልከል ሙሉ ሥልጣን አለው።

## በቃለ መጠይቁ ጊዜ ልዩ እርዳታ ስለማግኘት

በቃለ መጠይቁ ላይ በቋንቋ ችግር ምክንያት ወይም ድሮ በደረሰባቸው መጥፎ ገጠመኝ ምክንያት (ለምሳሌ እጅግ አሰቃቂ ገጠመኝ) ታሪካቸውን ማካፈል የሚከብዳቸው ሰዎች፣ የሚረዳቸው ከሆነ ሴት ጠያቂ ወይም ወንድ ጠያቂ እንዲቀርብላቸው ማስደረግ ይችላሉ። ሌሎች ልዩ ሁኔታዎች ካሉ በቃለ መጠይቁ ጊዜ እነሱን ለማሟላት ልዩ ጥያቄ ማቅረብ ይቻላል።

## አንድ ውሳኔ የተላለፈበትን ምክንያቶች መረዳት

የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትር እስራኤል ውስጥ የአንድ ስደተኛን ማመልከቻ ከከለከለ፣ ማመልከቻው ለምን እንደተከለከለ በዝርዝር የሚያስረዳ ደብዳቤ ለአመልካቹ/አመልካቿ ይሰጣል። አመልካቹ/አመልካቿ ደብዳቤው ላይ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ እስራኤልን ለቆ መሄድ ወይም ይግባኝ ማለት ይችላል/ትችላለች።

ሲከለከሉ ይግባኝ ማለት

አንድ/አንዲት ጥገኝነት ፈላጊ ማመልከቻው/ዋ ሲከለከልበት/ባት ይግባኝ ማለት ይችላል/ትችላለች። ማመልከቻው እንደተከለከለ የሚያስረዳው ደብዳቤ ስለ ይግባኝ አደራረግና ይግባኝ ለማስገባት ያለውን የጊዜ ግደብ መረጃ ይዟል። አብዛኛውን ጊዜ፣ ይህ በጽሑፍ መቅረብ ያለበት ይግባኝ፣ ጥገኝነት ፈላጊው/ዋ አዲስ መረጃ ከሌለው/ከሌላት በስተቀር ወይም በ RSD ቃለ መጠይቅ ጊዜ ጉዳዩ በግልጽ ያልተነገረ ሆኖ ካልተሰማው/ካልተሰማት በስተቀር ስኬታማነት አይኖረውም።

ይግባኙ እስኪመረመር ድረስ ጥበቃውን ማራዘም

RSD ውሳኔውን እስከሚያቀርብ ድረስ ጥገኝነት ፈላጊው/ዋ ጥበቃ ማግኘት ይችላል/ትችላለች፣ እስራኤል አገር ውስጥ መቆየትም ይችላል/ትችላለች።

ይግባኙም ከተከለከለ ግን UNHCR አመልካቹን መርዳት መቀጠሉን አይችልም። በዚህ ጊዜ አመልካቹ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትሩ በላከው ደብዳቤ ላይ ባለው ቀን ውስጥ እስራኤልን ለቆ መውጣት አለበት/አለባት። ይህንን አመራር የማይከተሉ አመልካቾች በኢሚግሬሽን ባለሥልጣኖች ይያዙና ከአገር እስኪወጡ በእሥራት ይቆያሉ።

የጥገኝነት ፈላጊዎች እሥራት

እስራኤል አገር ሲገቡ የታሠሩ ጥገኝነት ፈላጊዎች ከአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር የመጡ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ጋር፣ ከእስራኤል ወህኒ ባለሥልጣንና ከኢሚግሬሽን ፍርድ ቤት ዳኞች ጋር ይገናኛሉ። የጥበቃ ጥያቄ ከተደረገ በኋላና ምዝገባው ካለቀ በኋላ፣ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴሩ ወይም የኢሚግሬሽን ፍርድ ቤቱ ከእሥራት የመፈታት ውሳኔ ማድረግ ይችላሉ።

በሕገወጥ መንገድ መገኘት

በደንቡ UNHCR ጋር ወይም አገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር የተመዘገቡ ጥገኝነት ፈላጊዎች እስራኤል ውስጥ ያላችሁት በሕገወጥ ሁኔታ ነው ተብለው መታሠር የለባቸውም። UNHCR ጋር ወይም አገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር የተመዘገቡ ጥገኝነት ፈላጊዎች እስራኤል ውስጥ ያላችሁት በሕገወጥ ሁኔታ ነው ተብለው ቢታሠሩ UNHCRን ወዲያው ማስታወቅ ያስፈልጋል።

ጥገኝነት ፈላጊዎችና ስደተኞች ለአስተናጋጅ አገራቸው ግዳጅ አለባቸው፣ ሕጎቹንና ደንቦቹንም እንዲያከብሩ ይጠበቅባቸዋል። እስራኤል ውስጥ ወንጀል የሚፈጽሙ ጥገኝነት ፈላጊዎችና ስደተኞች በእስራኤል አገር ሕጎች መሠረት ይታሠራሉ፣ ፍርዱን እስከሚፈጽሙ ድረስም UNHCR ሊረዳቸው አይችልም።

እስራኤል ውስጥ ሥራ መሥራት

ጥገኝነት ፈላጊዎች በቀጥታ የሥራ ፈቃድ አይሰጣቸውም። ባብዛኛው የአገር ውስጥ ጉዳይ

ሚኒስቴር የሥራ ፈቃድ የሚሰጠው ኃይለኛ ማመልከቻ ላላቸው ጥገኝነት ፈላጊዎች ነው። ማመልከቻ ማስገባት ወይም ጥገኝነት ፈላጊ ሆኖ መመዝገብ አንድ ሰው እስራኤል ውስጥ “በቀጥታ” ሥራ መሥራት ይችላል ማለት አይደለም።

## <u>የጥገኝነት ፈላጊዎች ግዴታዎች</u>

ጥገኝነት ፈላጊዎች ከእስራኤል ባለሥልጣኖች ጋር ሁሉና ከUNHCR ጋር መተባበር አለባቸው። ጥገኝነት ፈላጊዎች ሰነዶቻቸውን፣ መታወቂያ ወረቀታቸውን፣ ፓስፖርታቸውን፣ ቪዛቸውን፣ ፈቃዳቸውንና ለቃለ መጠይቅ መጥሪያ ወረቀታቸውን በማናቸውም ጊዜ ላያቸው ላይ ይዘው መገኘት አለባቸው። የእስራኤል ባለሥልጣኖች አስቁመው ሰነድ ሲጠይቋቸው ማቅረብ ካልቻሉ እሥራት ያስከትላል።

**የመገናኛ መረጃ**

**አድራሻ** 119 Hahashmonaim St., Second floor, Tel Aviv (119 Hahashmonaim St.፣ 2ኛ ፎቅ፣ ቴል አቪቭ)

**ስልክ ቁጥር** 03-5167700

**ፋክስ** 03-5167800

**ኢሜል አድራሻ፦** ISRTE@unhcr.org

The Refugee Rights Program
The Elga Cegla Clinical Legal Education Programs
The Buchmann Faculty Of Law

התכנית לזכויות פליטים | የስደተኞች መብት መርሃ ግብር
התכניות לחינוך משפטי קליני ע"ש אלגה צלגה | ብሮችየኤልጋ ሴግላ የክሊኒክ ሕጋዊ ትምህርት መርሃ ግ
הפקולטה למשפטים ע"ש בוכמן | ባክማን የሕግ ፋከልቲ

# ስለ ጥገኝነት ፈላጊ አቋም መረጃና መብቶች

ሁሉ ሰው ጥገኝነት የመጠየቅ መብት አለው። በ1951 ዓ.ም. የወጣው ከስደተኞች ሁኔታ ጋር የተያያዘው ዓለማቀፍ ስምምነት ስደተኛ ተብሎ የሚጠራው ማን እንደሆነ ይገልጻል። ስምምነቱ እንደሚለው፦

> ስደተኛ ማለት “በዘር፣ በሃይማኖት፣ በዜግነት፣ በማህበራዊ አባልነት ወይም በፖለቲካ አስተያየት ምክንያት ስቃይ ይደርስብኛል ብሎ በመፍራት ከትውልድ አገሩ ውጪ ሆኖ በዚህ ፍራቻ ምክንያት እራሱን በዛ አገር ጥበቃ ሥር ማድረግ የማይችል ወይም የማይፈልግ ሰው ነው፣”

እስራኤል የስደተኞች ስምምነትን ፈርማለች፣ የጥገኝነት ጥያቄ የሚያቀርቡ ሰዎች ጥያቄያቸውን ለእስራኤል ባለሥልጣኖች ማቅረብ ይችላሉ። ጥያቄዎች የሚቀርቡት ለተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽነር ሲሆን፣ እሱም አመልካቾችን ቃለ መጠይቅ ይሰጥና አስተያየቱን ያዘጋጃል። የመጨረሻውን ውሳኔ የሚያስተላልፈው የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትር ነው። አልፎ አልፎ፣ በስደተኞች ስምምነት መሠረት ስደተኛ ላልሆኑና የአገራቸው ሁኔታ እንዲመለሱ ለማይፈቅድላቸው ሰዎች እስራኤል ጥበቃ ትሰጣለች።

አመልካቾች ሁሉ የሚከተሉት መደበኛ መብቶች አሏቸው፦

- የጥገኝነት ማመልከቻ ከሚያስፈልገው ማስረጃ ጋር ሁሉ አብሮ አያይዞ ለማስገባት፣ አንድ እሥር ቤት ያለ ሰው ለተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽነርም ማመልከቻ ማስገባት ይችላል፣
- የአንድ ሰው ማመልከቻ በሚጠናበት ጊዜ ከአገር እንዳይባረር ጥበቃ ለማግኘት፣ በእስራኤል ውስጥ ጥገኝነት ፈላጊዎች ማመልከቻ አሠራር ደንብ መሠረት፣ ጥገኝነት ፈላጊው ጥያቄውን በሚገልጽበት ጊዜ የሥራ ፈቃድ የማግኘት መብት አለው፣
- ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽነርና ከእስራኤል ባለሥልጣኖች ጋር ግንኙነት ያለው ጠበቃ መያዝ፣
- ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽነር ጋር በራስ ቋንቋ ቃለ መጠይቅ ማድረግ። ሴቶች ከፈለጉ ቃለ መጠይቁን ሴት እንድትሰጣቸው መጠየቅ ይችላሉ፣ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችም ቃለ መጠይቁ በተለይ ለነሱ እንዲዘጋጅ መጠየቅ ይችላሉ፣
- ማመልከቻው ከተከለከለ፣ አመልካቹ የተከለከለበትን ምክንያት በዝርዝር እንዲሰጠው የመጠየቅ መብት አለው፣
- የተከለከለውን ማመልከቻ ይገባኝ ብሎ ይግባኙ ግልጽ እስከሚደረግ ድረስ እስራኤል ውስጥ የመቆየት መብት፣
- የጥገኝነት ማመልከቻው ቢከለከልም፣ ለሰብዓዊ ምክንያቶች ሲባል እስራኤል ለመቅረት ማመልከቻ ማስገባት ይቻላል።

የስደተኞች መብቶች መርሃ ግብር በቴል አቪብ ዩኒቨርሲቲ የሚገኘው የሕግ ፋከልቲ ውስጥ ሆኖ የሚሠራ ሲሆን፣ ለጥገኝነት ፈላጊዎችና ስደተኞች በነጻ የሕግ እርዳታ ይሰጣል። በሚከተሉት ርእሶች በተመለከተ እርዳታ እንሰጣለን፦ ከእሥር ስለመፈታት፣ የጥገኝነት ማመልከቻ ስለማስገባት፣ የጥገኝነት ማመልከቻ አስገብቶ በሚከለከልበት ጊዜ ይግባኝ ስለማለት፣ ቤተሰብ ስለማገናኘትና ሌሎች የተለያዩ ስደተኞች በእስራኤል ውስጥ ሳሉ የእለት ተእለት ኑሯቸው ላይ ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ ችግሮች።

የስደተኞች መብቶች መርሃ ግብርን በሚከተለው ስልክ ቁጥሮች መገናኘት ይቻላል፦ 03-6405264 ወይም 03-6406772 ወይም በፋክስ፦ 03-6407422። እሥር ቤት ያሉ ሰዎች የስደተኛ ሠራተኞች መረጃ መስመር እንዲገናኙን ቢጠይቁ፣ እሥር ቤት መጥተን ማነጋገር እንችላለን። አስቀድማችሁ ቀጠሮ ሳትይዙ አባካችሁ ቢሮዋችን አትምጡ። የሚቀርቡልን ጥያቄዎች ሁሉ ማስተናገድ አንችልም፣ ለዚህም በቅድሚያ ይቅርታ እንጠይቃለን።

מוקד סיוע לעובדים זרים (ע"ר)

**Hotline for Migrant Workers**

"You shall not wrong a stranger, nor oppress him, for you were strangers in the land of Egypt", *Exodus 22:20*

## ለስደተኛ ሠራተኞች የመረጃ መስመር

"እናንተ በግብጽ ምድር ስደተኞች ነበራችሁና ስደተኛውን አትበድለው፣ ግፍም አታድርግበት።" (ዘጸአት 22:21)

# እሥር ላይ ያሉ ጥገኝነት ፈላጊዎች ስላሏቸው መብቶችና መረጃ

የስደተኛ ሠራተኞች መረጃ መስመር (HMW) መንግሥታዊ ያልሆነ፣ የስደተኛ ሠራተኞችን፣ በሕገወጥ መንገድ መጓጓዝ የደረሰባቸው ሰዎችንና የጥገኞችን መብት ለመጠበቅ የሚሠራ የሰብዓዊ መብቶች ድርጅት ነው። ከHMW ስራዎች ውስጥ የሚከተሉት አሉበት፦ ስለ መብቶች መረጃ መስጠት፣ ሕጋዊ ምክርና ጥብቅና፣ ሕዝቡ ስለ ጉዳዩ ያለውን ዕውቀት ከፍ ማድረግ እንዲሁም የኢሚግሬሽን መመሪያን መገፋፋት። እሥራት ላይ ላሉ ሰዎች ትብብር እናቀርባለን።

ወደ እስራኤል ውስጥ መግቢያ ሕግ የሚባለው ሕግ አገር ውስጥ የገባው ሐገወጥ በሆነ መንገድ ነው ተብሎ የሚጠረጠርን ሰው ማሠር ይፈቅዳል። ጥገኝነት የሚፈልጉ ከሆነ

እስራኤል ውስጥ የሚገኘውን የ UNHCR ቢሮ በተቻለ መጠን በቶሎ መገናኘትዎ በጣም አስፈላጊ ነው። በሆነ ምክንያት ታሥረው ከሆነ፣ የሚከተሉት መብቶች አልዎት፦

## በቁጥጥር ሥር በሚውሉበት ጊዜ ያሉዎት መብቶች፦

- የፍተሻ የፍርድ ቤት ማዘዣ ከሌላቸው በስተቀር ፖሊሶች ቤትዎ ውስጥ የመግባት መብት
- የላቸውም። ፖሊሶቹ ቤቱ ውስጥ ላሉት ሰዎች ማዘዣውን መስጠት አለባቸው። ትእዛዙ
- የተጻፈው እርስዎ በሚገባዎት ቋንቋ መሆን አለበት፣ የቤቱንም ትክክለኛ አድራሻ መያዝ አለበት።

በሚይዙበት ጊዜ ምንም ዓይነት ኃይል መጠቀም የለባቸውም። አልተባበርም ብለው ቢያስቸግሩ፣ ፖሊሱ አስፈላጊውን ኃይል መጠቀም ይችላል።

- በቁጥጥር ሥር እንደዋሉ ለማሳወቅ አንድ የስልክ ጥሪ ማድረግ ይፈቀድልዎታል።
- ሰው በቁጥጥር ሥር ሲውልና ሲለቀቅ ያለው አስተዳደራዊ ሥርዓት
- የጠረፍ ፖሊስ፦ በቁጥጥር ሥር በዋሉ በ24 ሰዓት ውስጥ፣ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ወኪል የሆነ የጠረፍ ፖሊስ ፊት ቀርበው ጉዳዩ በፍርድ ቤት ይሰማል። ይህ ፖሊስ ጉዳዮን ይመረምራል፣ ከአገር የማባረር ወይም የእሥራት ፍርድ የመስጠት ስልጣን አለው። ከእሥር የመፍታትም ስልጣን አለው።
- አስተዳደራዊ ልዩ ፍርድ ቤት፦ በቁጥጥር ሥር በዋሉ ከአራት ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የእሥር ቤት ውስጥ የሚሰራ አስተዳደራዊ ልዩ ፍርድ ቤት ፊት መቅረብ አለብዎት። ፍርድ ቤቱ የእሥራቱን ውሳኔ የመቆጣጠርና ከእሥር የመልቀቅ ስልጣን አለው።
- ከአገር የመባረር ትእዛዝ ተላልፎብዎ ከሆነ የትእዛዙን ግልባጭ በቋንቋዎ የማግኘት መብት አልዎት።
- የመባረሩ ትእዛዝ ከደረስዎት በኋላ ይግባኝ ለማለት 72 ሰዓት አልዎት። በዚህ ጊዜ ይግባኝዎን ለጠረፍ ፖሊሱ ማቅረብ ይችላሉ።
- በቁጥጥር ሥር ከመዋልዎ በፊት ለጥገኝነት አመልክተው ከነበረና ይህንን የሚገልጽ ሰነዶች ይዘው ከሆነ (ከUNHCR ወይም ከአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር)፣ በቁጥጥር ሥር የሚያውልዎትን ፖሊስ፣ የጠርፍ ፖሊሱንና አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱን ስለዚህ ጉዳይ ማሳወቅዎ በጣም አስፈላጊ ነው።
- ጥገኝነት መጠየቅ ፈልገው ከነበረና በቁጥጥር ሥር ከመዋልዎ በፊት በሆነ ምክንያት

UNHCRን ሳይገናኙ ቀርተው ከሆነ፣ ወደ አገርዎ መመለስ እንደሚፈሩ ለማንኛውም ለሚያገኙት ባለሥልጣን መንገር ይችላሉ (ለፖሊስ፣ ለጠረፍ ፖሊስ፣ ለልዩ ፍርድ ቤት፣ ለእሥር ቤት ባለስልጣን፣ ወዘተ)።

- ጥገኝነት ፈላጊዎች ጉዳያቸው በምርመራ ሥር ሳለ ከአገር መባረር የለባቸውም።።

<u>እሥር ቤት ሳሉ የሚከተሉት መብቶች አሉዎት፦</u>

<u>በልኩ ስልክ መጠቀም መቻል።</u>

- የ UNHCR ተወካዮች፣ ጠበቃና የስደተኛ ሠራተኞች የመረጃ መስመር ፈቃደኛ ሠራተኞች ማግኘት።
- በቀን ሶስት ጊዜ መጋቢነት ያለው ምግብ የማግኘት፣ የግል ንጽሕና መጠበቂያ ቁሳቁሶች እንደ ሳሙና፣ ሻምፖና የጥርስ ሳሙና የመሳሰሉት፣ ለወቅቱ የሚሆን ልብስ (የራስዎ ከሌልዎት)፣ እና ብርድ ልብሶች።
- አስፈላጊውን ሕክምና የማግኘት።
- ከእስራኤላዊ ወንጀለኛ እሥረኞች ተለይቶ የመታሠር።
- ቢያንስ በቀን አንድ ሰዓት ከክፍልዎ ወጥተው የእሥር ቤቱ ግቢ ውስጥ የመናፈስ።
- በሚለቀቁበት ጊዜ ሁሉን የግል ዕቃዎችዎንና ሰነድዎችዎን መልሶ የማግኘት።

<u>የመለቀቅ ቅድመ ሁኔታዎች</u>

- ከሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱን እንደሚያሟሉ ካመኑ፣ የጠረፍ ፖሊሱም የእሥር ቤቱ አስተዳደራዊ ልዩ ፍርድ ቤቱም እርስዎን የመልቀቅ ስልጣን አላቸው፦
- እስራኤል ውስጥ የሚኖሩት በፈቃድ ሲሆን በቁጥጥር ሥር መዋልዎ ሕጋዊ አይደለም።
- ከአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትር ውሳኔ በመጠባበቅ ላይ ያሉ ጥገኝነት ፈላጊ ነዎት።
- እስራኤል ውስጥ ያሉት በስሕተት ወይም ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ወይም በርስዎ ጥፋት አይደለም፣ በተወሰነ ቀን ውስጥም እስራኤልን ለቅቀው ሂያጅ ነዎት።
- እስራኤልን በተወሰነ ቀን በራስዎ ለቅቀው ሂያጅ ነዎት፣ ካልሆነም በቀላሉ ሊገኙ ይችላሉ።
- እሥር ቤት መግባት ጤናዎን ሊያውክ ይችላል።
- ለመለቀቅዎ ልዩ ሰብዓዊ ምክንያቶች አሉ።
- እርስዎ ቢታሠሩ፣ የእርስዎ ኃላፊነት የሆነ ትንሽ ልጅ ያለጠባቂ ይቀራል።

- በቁጥጥር ሥር ከዋሉ ከ60 ተከታታይ ቀናት በላይ ሆኖታል።
- እነዚህ ሁሉ ቅድመ ሁኔታዎች የሚሠሩት ከባለስልጣኖች ጋር ሁሉ ተባብረው ከሆነና፣ የደህንነት ወይም የሕዝብ ጤና ላይ ችግር የማያስከትሉ ከሆነ ነው።

ከነዚህ መብቶች ውስጥ ማናቸውም ተጥሰዋል ብለው የሚያምኑ ከሆነ፣ እባክዎን ይገናኙን። የስደተኛ ሠራተኞች የመረጃ መስመር ድርጅት ፈቃደኛ ሠራተኞች የሚሠሩት ለሚከተሉት ነው፦

- እሥር ላይ ያሉ ጥገኝነት ፈላጊዎችን መብቶጭ መጠበቅ።
- የታሠሩ ጥገኝነት ፈላጊዎችንና ቤተሰቦቻቸውን ከእሥር መለቀቅ ማፋጠን።
- በእሥር ቤት ወይም በሌላ ቦታ ያሉ ዘመዶችንና እውቂያ ያልዎትን ሰዎች ማግኘት።

በታሠሩ ጥገኝነት ፈላጊዎችና በ UNHCR ተወካዮች እንዲሁም ሌሎች ለጥገኝነት ፈላጊዎች ተጨማሪ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች መሃል ግንኙነት መፍጠር።
አንዳንድ ጉዳዮች ላይ፣ አስፈላጊ ከሆነ፣ የስደተኛ ሠራተኞች የመረጃ መስመር ድርጅት የሕጋዊ ምክርና የጥብቅና አገልግሎት ይሰጣል።

ፈቃደኛ ሠራተኞቻችን የማሲያሁ እሥር ቢትን በሳምንት ብዙ ጊዜ ሄደው ይጎበኛሉ፣ ሌሎች እሥር ቤቶችንን ደሞ በየሳምንቱ ወይም በየሁለት ሳምንቱ ሄደው ይጎበኛሉ። የሚታወቁት በስልክ ካርዳቸው ወይም የስደተኛ ሠራተኞች መረጃ መስመር ምልክት ባለው ሸሚዝ በመልበሳቸው ነው።
እንዲሁም የስደተኛ ሠራተኞች የመረጃ መስመር ጋር በ ስልክ ቁጥር 03-5602530 መደወል ይችላሉ።
ቴል አቪብ ውስጥ በ 75 Nahalat Binyamin St. አድራሻ የሚገኘው ቢሮዋችን ከእሁድ እስከ ሐሙስ ከ 9፡00 ሰዓት እስከ 17፡00 ሰዓት ክፍት ነው።

## መብቶችዎን እንዲያስከብሩ ልንረዳዎት እንፈልጋለን። አገልግሎቶቻችን ነጻ ናቸው።

Kav LaOved קו לעובד ע"ר عنوان للعامل

# ሥራ መስራትን በተመለከተ ጥገኝነት ፈላጊዎችና ስደተኞች ያላቸው መብቶችና መረጃ

ካብ ላኦቬድ (የሠራተኞች መረጃ መስመር) መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን ሕግ ነክ ምክሮችና እርዳታ በመለስተኛ ዋጋ የሰጣል። እርዳታው የሚሰጠው እስራኤል ውስጥ ለሚሠሩ ሠራተኞች፣ ስደተኛ ሠራተኞችን ጨምሮ፣ ጥገኝነት ፈላጊዎችና ለስደተኞች ነው። ሥራንና ደምወዝን በተመለከተ ችግር ካጋጠምዎት ሐሙስ ሐሙስ ከ 17፡00 ሰዓት እስከ 20፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ቴል አቪብ በ 17 Y.L. Peretz Street አድራሻ የሚገኘው ቢሮዋችን (የድሮው መሃከለኛው አውቶቡስ ጣቢያ አጠገብ) ጋር እንዲመጡ እንጋብዝዎታለን። እባክዎን መታወቂያ ሰነድና አሁን ካልዎት ሥራ ጋር የተያያዙትን ወረቀቶች ሁሉ ይዘው ይምጡ (የሥራ ካርድ፣ የደምወዝ ቁራጭ፣ የቀጣሪ የድርጅት መታወቂያ ካርድ፣ የራስዎ ማስታወሻ፣ ወዘተ.)

## ሥራንና ደምወዝን በተመለከተ ጠቃሚ ምክሮች

### አዲስ ሥራ ሲጀምሩ፦

1. ቃል የተገባልዎትን ደምወዝና የሥራ ሁኔታ የሚገልጽ ሰነድ ቀጣሪዎ በጽሑፍ እንዲሰጥዎት ይጠይቁ።
2. ስለ መሥሪያ ቤትዎ በተቻለ መጠን ብዙ መረጃ ይጻፉ። ለምሳሌ ሬስቶራንት ውስጥ ሥራ ከጀመሩ፣ የሬስቶራንቱን ስም፣ የአስተዳዳሪውን ሙሉ ስም (የመጀመሪያና

የአባት ስም)፣ ሬስቶራንቱ ጋር የላክዎትን የሥራ አስቀጣሪ ሙሉ ስም፣ የሬስቶራንቱ አድራሻና የአስቀጣሪው ድርጅት አድራሻ ይጻፉ። ከተቻለ አስተዳዳሪዎቹን የሥራ ድርጅት ካርድ ይጠይቁ።

3. ደምወዝ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ማን እንደሆነ ያጣሩና ሥራውን ከመጀመርዎ በፊት ከእርሱ/እርሷ ጋር በክፍያው ይስማሙ።
4. ሕጋዊ ፓስፖርት የሌላቸው ስደተኞችና ሕጋዊ ፓስፖርት ወይም ፎቶዋቸው ያለበት የተባበሩት መንግስታት የሰጣቸው የጥበቃ ሰነድ የሌላቸው ሱዳናዊ ስደተኞች እስራኤል ውስጥ የባንክ ሒሳብ መክፈት አይችሉም። የባንክ ሒሳብ መክፈት የማይችሉ ከሆነ ለቀጣሪዎ በግልጽ መንገር አለብዎት፣ በየወሩ ደምዎዝዎን በጥሬ ገንዘብ እንዲከፍልዎትም ያሳስቡ። ከተቻለ ቀጣሪዎ ይህንን ስምምነት ስለ ደምዎዝዎና ስለ ሥራ ሁኔታዎ የሚገልጸው ሰነድ ውስጥ እንዲያስገባው ይጠይቁ።
5. በተቋራጭ በኩል ሥራ ከማግኘት ይልቅ በራስዎ ወይም በጓደኞችዎ አምካኝነት ሥራ ለማግኘት ይሞክሩ። ልምዳችን የሚያሳየው አብዛኛውን ጊዜ ችግሮች የሚፈጠሩት አስቀጣሪዎች ደምዎዝ አልከፍልም እያሉ ነው።

<u>ተቀጥረው በሚሠሩበት ጊዜ፥</u>

1. የሥራ ሰዓት መቆጣጠሪያ ሰዓት መስሪያ ቤትዎ ውስጥ ቢኖርም በራስዎ ደብተር ውስጥ በየቀኑ ሥራ የጀመሩበትንና የጨረሱበትን ሰዓት ይጻፉ። በየወሩ የተከፈልዎትን ደምወዝ መጠን እንዲሁም የተቀበሉበትን ቀን ይጻፉ። ተጨማሪ ክፍያ ከደረስዎትም ይጻፉት (ለምሳሌ የመጓጓዣ ገንዘብ፣ ቅድሚያ ክፍያ፣ ብድር፣ ወዘተ)
2. ለቀጣሪዎ የሚሰጡትን የሥራ ሰዓቶች መዝገብ ግልባጭ ያስቀምጡ። የደምወዝ ክፍያ ደረሰኝ የሚሰጥዎት ከሆነ በደንብ ያስቀምጧቸው።
3. ልብ ይበሉ፥ ወደ ሥራ ሲሄዱና ከሥራ ወደ ቤት ሲመለሱ የሚያጠፉት ጊዜ እንዲሁም በሥራ መሃል እረፍት ላይ የሚያጠፉት ጊዜ እንደ ሥራ ሰዓት አይቆጠሩም፣ ክፍያም አይኖራቸውም።

<u>ከሥራ ሲለቁ፥</u>

1. ሥራዎን መልቀቅ ከፈለጉ፣ ቀጣሪዎን አስቀድመው እንዲያስታውቁ እንመክራለን። አንድ ሠራተኛ ሥራውን ለቅቆ ከመሄዱ በፊት በቅድሚያ ማስታውቅ አለበት። አንድ ሠራተኛ እንደ ደንቡ መሠረት በቅድሚያ ሳይናገር ሥራውን ቢለቅ፣ ቀጣሪው የሚቀሩትን ቀኖች ለማስተካከል ከደምወዙ ገንዘብ መቀነዝ ይችላል፣ በመጀመሪያው ዓመት ውስጥ ለሠራባቸው ለእያንዳንዱ የሥራ ወር አንድ ቀን መቀነስ ይችላል።
2. ሥራዎን በሚለቁበት ቀን ቀጣሪዎ ደምወዝዎን እንዲከፍልዎት መጠየቅ ይችላሉ፣ ሆኖም አብዛኛውን ጊዜ ቀጣሪው ይህን ማድረግ አይችልም ምክንያቱም የሒሳብ

ሲስተሙ በኮምፒዩተር የሚሠራ ሲሆን ደሞወዞችን ማዘጋጀት የሚችለው በእያንዳንዱ ወር ከዘጠነኛው ቀን አስቀድሞ ብቻ ነው። ልብ ይበሉ እርስዎ ቀደም ብለው ሥራዎን ቢለቁም ቀጣሪዎ ከሚቀጥለው ወር ከ9ኛው ቀን በፊት ደምዎዝዎን የመክፈል ግዴታ የለበትም።

ስለ ሥራና ስለ ደምወዝ መረጃ

እነዚህ ወረቀቶች ላይ ያለው መረጃ ባብዛኛው በሰዓት የሚከፈላቸውን ሠራተኞች የሚመለከት ነው፣ ምክንያቱ አብዞኞቹ እስራኤል ውስጥ ያሉ ጥገኝነት ፈላጊዎችና ስደተኞች በዚህ መንገድ ነው የሚከፈላቸው።

ከዚህ በታች የተጠቀሰው ዝቅተኛ ክፍያ ከኦገስት 2008 ጀምሮ ትክክለኛው ክፍያ ነው፣ አልፎ አልፎ እንደ መንግሥት ውሳኔም ይቀየራል (መጠኑ ሁልጊዜ ከፍ እያለ ይሄዳል!)።

እስራኤል ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩ ሠራተኞች በሙሉ (የሥራ ፈቃድ ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም) የሚከተሉት መብቶች አሏቸው፦

የሠራተኞች መብት (በሰዓት ለሚከፈላቸው ሠራተኞች) 12.08

ካቭ ላኦቬድ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን ለሠራተኞች ምክር፣ መመሪያና ሕጋዊ እርዳታ ይሰጣል። የሚከተሉት መብቶች በእስራኤል ሕግ ለሁሉም የእስራኤል ሠራተኞች እስራኤላዊም ይሁኑ የውጪ ዜጎች የተሰጡ ናቸው (ቪዛ ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም)፦

| | |
|---|---|
| ዝቅተኛ ክፍያ | 3,850 NIS ለሙሉ ጊዜ ሥራ (186 ሰዓት በወር)፣ በሰዓት 20.70 NIS። |
| የክፍያ ጊዜ | ክፍያ ወር በገባ ከዘጠነኛው ቀን ባላለፈ መከፈል አለበት (ላለፈው ወር)። |
| ከሥራ ሰዓት በላይ ለተሠራ ሰዓት ክፍያ | በቀን 8 ሰዓት ከተሠራ በኋላ እያንዳንዱ ተጨማሪ ሰዓት። ከሥራ ሰዓት በላይ ክፍያ የሚታሰበው ለእያንዳንዱ ቀን የተሠራ ሰዓት ነው (ከሌሎች ቀኖች ሰዓት ላይ የሚቀነስ አይደለም)። ክፍያ፦ የመጀሪያዎቹ ሁለት ሰዓታት - 125% (በሰዓት 25.8 NIS)፣ ከሁለቱ ሰዓት ውጪ ማንኛውም ሌላ ሰዓት - 150% (በሰዓት 31 NIS)። |

| | |
|---|---|
| የሰሩበትን ሰዓቶች መመዝገብ | ድንገት ከቀጣሪዎ ጋር አለመስማማት ቢፈጠር፣ በየቀኑ የሰሩበትን ሰዓት መጻፍ አስፈላጊ ነው (የጀመሩበትንና የጨረሱበትን ሰዓት)። |
| የመጓጓዣ ወጪ | ወደ ሥራ ለመሄድና ከሥራ ሲመለሱ ለመጓጓዣ ያወጡትን ገንዘብ ቢበዛ በቀን እስከ 21.14 NIS ድረስ ቀጣሪዎ መካስ አለበት። |
| ሳምንታዊ የእረፍት ቀን | በየሳምንት 36 ተከታታይ የእረፍት ሰዓታት ማግኘት አለብዎት፣ በሃይማኖትዎ መሠረት የሚወስዱትን የእረፍት ቀን ጨምሮ። በእረፍት ቀንዎ ከሰሩ በቀን የሚከፈልዎትን 150% ማግኘት አለብዎት፣ በተጨማሪም ሌላ የእረፍት ቀን ማግኘት አለብዎት። |
| ዓመታዊ የእረፍት ጊዜ | ሥራ ሲጀምሩ ለመጀመሪያዎቹ አራት ዓመታት በዓመት ሁለት ሳምንት የእረፍት ጊዜ ያገኛሉ (ሳምንታዊ የእረፍት ቀንዎን ጨምሮ)። ስለዚህ ለምሳሌ አንድ በሳምንት አንድ ቀን የሚሠራና እያንዳንዱ ጊዜ 150 NIS የሚከፈለው ሠራተኛ፣ በዓመት ሁለት ቀን ተከፍሎት የእረፍት ቀን መውሰድ ይችላል (150 x 2 የእረፍት ቀን = 300 NIS)። ከአራት ዓመት በኋላ፣ በዓመት የሚያገኙት የእረፍት ቀኖች ይጨምራሉ። |
| በዓሎች | ሶስት ወር ከሠሩ በኋላ እንደ ኃይማኖትዎ በዓመት ዘጠኝ የበዓል ቀኖች ክፍያ ማግኘት ይጀምራሉ (እነዚህ ቀኖች ሳምንታዊ የእረፍት ቀንዎ ጋር እስካልተጋጩ ድረስ)። አንድ በዓል የሚውለው በሥራ ቀንዎ ከሆነ፣ መደበኛ ክፍያዎን በበዓሉ ቀን ያገኛሉ። በበዓል ሥራ የሚሠሩ ከሆነ የሚያገኙት ክፍያ ከመደበኛ ክፍያዎ 150% ነው፣ በተጨማሪም የበዓል ቀን ክፍያውን ያገኛሉ (ባጠቃላይ 250%)። |

| | |
|---|---|
| የማገገሚያ ክፍያዎች | አንድ ሙሉ ዓመት ያገለገለ ሠራተኛ በቀን ውስን 331 NIS የማገገሚያ ክፍያ የማግኘት መብት አለው። ለመጀመሪያው ዓመት - 5 ማገገሚያ ቀኖች፣ ለሁለተኛውና ለሶስተኛው ዓመት - 6 ማገገሚያ ቀኖች፣ ከአራተኛው እስከ አሥረኛው ዓመት - 7 ቀኖች ያገኛል። በከፊል ለሚሰሩ ሠራተኞች ሒሳቡ የሚሰራው እንደ ሥራው ቆይታ እየታየ ነው። |
| የሥራው ቆይታ ሒሳብ | በሳምንት የሚሠሩት ሰዓት በ 4.3 ይባዛል (በአንድ ወር ውስጥ ያሉት ሳምንታት) ከዛም በ 186 ይካፈላል (የሙሉ ጊዜ ሥራ ላይ በወር ውስጥ ያሉት ሰዓታት)። |
| የሕመም ክፍያ | ከታመሙና ከዶክተር ወረቀት አምጥተው ለቀጣሪዎ ከሰጡ ቀጣሪዎ ደምወዝዎን መክፈል አለበት። ለመጀመሪያው የሕመም ቀን አይከፈሉም፣ ለሁለተኛውና ለሶስተኛው ቀኖች 37.5% ይከፈልዎታል፣ ከአራተኛው ቀን ጀምሮ የቀን ደምወዝዎን 75% ይከፈልዎታል። |
| የመለያያ/ ከሥራ ሲለቁ ክፍያ | አንድ ዓመት ሥራ ከሰሩ በኋላ ከሥራዎ ከተባረሩ ወይም የሥራ ሁኔታው ቀዝቀዞ ቢያልቅ፣ በጤና መታወክ ምክንያት፣ ልጅ በመውለድ ምክንያት ወይም ደምወዝዎንና ማህበራዊ መብቶችዎን ሳያገኙ ከቀሩ የመለያያ ክፍያ ማግኘት አለብዎት። የክፍያው ጊዜ፦ ሥራዎን ሰርተው ሲያበቁ። ሒሳብ፦ የአንድ ወር ደምወዝ በሰሩበት ዓመታት ተባዝቶ (በከፊል የሰሩበት ዓመት ተጨምሮ)። |

| | |
|---|---|
| ከመባረርዎ በፊት ማስታወቂያ መስጠት/መልቀቅ | እርስዎና ቀጣሪዎ ከመባረርዎ ወይም ከመልቀቅዎ በፊት በጽሑፍ ማስታወቂያ መስጣጠት አለባችሁ። የሚሰጠው ማስታወቂያ ብዛት እንደሰሩበት ጊዜ ይለያያል፦ በመጀመሪያው ዓመት - ለእያንዳንዱ ወር 1 ቀን፣ በሁለተኛው ዓመት - 14 ቀንና ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ወር ግማሽ ቀን፣ በሶስተኛው ዓመት - 21 ቀንና ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ወር ግማሽ ቀን፣ ከሶስት ዓመት በኋላ አንድ ወር። ክፍያ፦ አስቀድሞ ማስታወቂያ የማይሰጠው ሰው ለዛኛው ሰው የጊዜውን መደበኛ ደምወዝ የሚያክል ካሳ ክፍያ መስጠት አለበት። |
| ለከፊል ዓመት መብቶች | ለአንድ ሙሉ ዓመት ሰርተው ባይሆንም ሙሉ የዓመት እረፍትዎንና የበዓል ቀኖችዎን የማግኘት መብት አልዎት (በከፊል ያገኛሉ)። ለመለያያ ክፍያና ለማገገሚያ ክፍያ፣ ከአንድ ዓመት በላይ ሰርተው እስከሆነ ድረስ እነሱንም በከፊል የማግኘት መብት አልዎት። |
| እርግዝናና እናትነት | ነፍሰጡር ሴትን ከሥራ ማባረር በሕግ አይፈቀድም። ልጅ ሲወልዱ ሆስፒታል የሚቆዩበት ሊከፈልልዎት ይገባል፣ እንዲሁም ለወለዱ የሚሰጥ የአንድ ጊዜ ክፍያና ሶስት ወር ተከፍልዎት የአራስነት እረፍት ከብሔራዊ ዋስትና (National Insurance) ያገኛሉ። ሆስፒታል ሲመጡ ፓስፖርትዎንና የእርግዝናዎን ምረመራ ሰነዶች በሙሉ ይዘው መምጣት ያስፈልጋል። |
| የጤና ዋስትና | ቀጣሪዎ የጤና ዋስትና እንዲያገኙ ማስተባበር አለበት፣ ከደምወዝዎም በወር ከ106 NIS ያልበለጠ መቁረጥ ይችላል። የጤና ዋስትናዎን በራስዎ ማስተባበር ከፈለጉ ማድረግ ይችላሉ (አሁን ሃሬል ዋስትና ብቻ ነው ያለው 7547020-03) |

| | |
|---|---|
| ብሔራዊ ዋስትና | ቀጣሪዎ በብሔራዊ ዋስትና በኩል ዋስትና ሊያሲዝዎት ይገባል። ለብሔራዊ ዋስትና ክፍያ የተደረገበትን ደረሰኝ ግልባጭ እስከነ ቀጣሪዎ ሰነድ ቁጥር ማግኘትዎ አስፈላጊ ነው፣ ድንገት ሆስፒታል ቢገቡ ይህ አስፈላጊ ነው (ሥራ ላይ አደጋ ቢያጋጥም ወይም ልጅ በሚወልዱበት ጊዜ)። |
| ሕክምና | የሚያገኙት ሕክምናዎች በሙሉ የግል ዋስትናዎ ይሸፍናቸዋል፣ ከሥራ አደጋዎችና ከወሊድ በስተቀር፣ እነዚህ ብሔራዊ ዋስትና ነው የሚሸፍናቸው። በድንገተኛ ጊዜ የጤና ዋስትና ወይም ቪዛ ባይኖርዎትም በማንኛውም ሆስፒታል ሕክማና ማግኘት ይችላሉ (በኋላ ግን መክፈል ይኖርብዎታል)። |
| አስገድዶ መድፈር | አስገድዶ መድፈርና ማስፈራራት በእስራኤል ሕግ መሠረት ሐገወጥ ነው። ይህም አንዲት ሠራተኛ ግንኙነት ካላደረገሽ አባርርሻለሁ ብሎ ማስፈራራት፣ የጾታ ጥቃቶችንና ጥያቄዎችን ጨምሮ ነው። ማንም ይህን ዓይነት ጥቃት የደረሰበት ሠራተኛ ካሽ ላኦቬድ ጋር መሄድ/መደወል ይችላል። |

አቤቱታዎ የሚመለከተው ሳይከፈለ የቀረ ደምወዝን ከሆነ፣ እባክዎን ሥራ ልማት ሚኒስቴር (Ministry of Labour) የሚገኘው ጠበቃ አይሪስ ማያን ጋር በስልክ ቁጥር 050-6240546 ይደውሉ።

ARDC
המרכז לקידום פליטים אפריקאים
African Refugee Development Center

ARDC

**የአፍሪካ ስደተኞች እድገት ማዕከል**

# ለጥገኝነት ፈላጊዎችና ለስደተኞች ሰብዓዊ እርዳታ

ስለ ARDC

ARDC ማለት እስራኤል ውስጥ ጥበቃና ደህንነት የሚፈልጉ የአፍሪካ ስደተኞችን ለመርዳት፣ ለመደገፍና ለማጠናከር በ2004 ዓ.ም. የተቀረቀረ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው። የARDC ሥራዎች የሚያተኩሩት የግለሰብ አማካሪነት፣ ሰብዓዊ እርዳታ፣ ማስተማርና የማህበረሰብ እድገት ላይ ነው። ስደተኞችና ጥገኝነት ፈላጊዎች መብታቸው እንዲከበርና የእስራኤል የጥገኝነት አመራር ሰብዓዊና ትክክለኛ እንዲሆንም ድጋፉን ይሰጣል።

ARDC የሚከተሉትን አገልግሎቶች ይሰጣል፦

የግለሰብ እርዳታ፦ የጥግኝነት ማመልከቻን፣ ጤንነትን፣ መኖሪያ ቤትን፣ ሥራን፣ ትምህርትን፣ ማህበራዊና ስነ አእምሮ ሕክምናን በተመለከተ አንድ ለአንድ ምክርን፣ ጥቆማና ሌሎች እርዳታዎችን መስጠት። ለስደተኛ ልጆች፣ ለወላጆቻቸውና ለአዋቂዎች የእንግሊዝኛና የእብራይስጥ ቋንቋ ትምህርት፣ የግል አስተማሪና ምክር።

ሰብዓዊ እርዳታ፦ ARDC ለቤት አልባ ቤተሰቦች፣ ሴቶች፣ አዛውንቶችና ጠባቂ የሌላቸው ለአካለ መጠን ላልደረሱ ልጆች ቴል አቪቭ ውስጥ መጠለያዎች አሉት። ሰብዓዊ እርዳታ፣ መኖሪያ ቦታ፣ ሕክምና፣ ምግብና ድንገተኛ ቁሳቁሶች ለስደተኞች ይሰጣል።

ማህበራዊ እድገት፦ ARDC ስደተኛ ማህበረሰቦችን በተመለከተ የመሪነት፣ መልዕክት ማስተላለፍ፣ ማህበረሰባዊ ዕቅድ ማውጣት፣ የገንዘብ አስተዳደርንና የድጋፍ ርዕሶችን ድጋፍ ይሰጣል።

ማህበረሰባዊ ግንኙነትና በፈቃደኝነት መሥራት፦ ARDC ከእስራኤል ማህበረሰብ ጋር መቀላቀልና መገናኘት የሚያስችሉና የባሕል ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችሉ ድልድይ የሆኑ መርሃ ግብሮችን ያመቻቻል። ይህም ሰፊው የእስራኤል ማህበረሰብ ውስጥ የስደተኛ መርሃ ግብሮች ጋር በፈቃደኝነት መሥራትን ማስተዋወቅና ማስፋፋትን ይጨምራል።

# ይገናኙን

ARDC - African Refugee Development Center
52 Golomb St. 2nd floor, Tel Aviv
(near the new central buss station)

ስልክ ቁጥር፦ 054 638 8633 | (እንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛ)፣ 054 681 6333 (አማርኛ፣ እንግሊዝኛ) | ፋክስ፦ +972 672 0558
ኢሜል፦ info@ardc-israel.org | www.ardc-israel.org

# ለጥገኝነት ፈላጊዎችና ለስደተኞች ሰብዓዊና ስነ አእምሮ ነክ እርዳታ መረጃ

Assaf (አሳፍ) የሚሠራው እስራኤል የተጠለሉትን ስደተኞችና ጥገኝነት ፈላጊዎችን ለመጠበቅ ነው። በዓለማቀፍ ሕግና በግብረ ገብነት መሠረት መብታቸው እንዲሻሻልና ኦፊሲዬላዊና ማህበራዊ ሁኔታቸው እንዲጠበቅ የሚሞክር ድርጅት ነው። የAssaf ጥረት ስደተኞችና ጥገኝነት ፈላጊዎች የማህበራዊ፣ የገንዘብና የስነ አእምሮ ችግሮች ሲያጋጥሟቸው መቋቋም እንዲችሉ ለማድረግ፣ እስራኤል ውስጥ ያሉ ስደተኞች ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥና የማይጎዳና ሰብዓዊ የሆነ መጠለያ ለማቅረብ ነው።

Assaf እስራኤል ውስጥ ያሉ ስደተኞችና ጥገኝነት ፈላጊዎችን ይረዳል። ዋና መንቀሳቀሻ ማዕከሎቹ በቴል አቪብ፣ ኤይላትና አራድ ይገኛሉ - እነዚህ አካባቢዎች ስደተኞች በብዛት የሚገኙባቸው አካባቢዎች ናቸው።

Assaf ስደተኞችን በተመለከተ የሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች የሚከተሉትን የያዘ ነው፦

1. ለግለሰቦችና ለቤተሰቦች እርዳታ
   - መጀመሪያ እስራኤል ገብተው ሲላመዱ እርዳታና ትብብር
   - መርሃ ግብሮችና ድርጅቶች ለመገናኘት ጥቆማና እርዳታ
   - የሕክምና አገልግሎቶችን ለመገናኘት ጥቆማና እርዳታ
   - ሥራ የማፈላልግ እርዳታ

- የስነ አእምሮ እርዳታ ካስፈለገ
- ማስታረቅ

2. ልጆች
- ለልጆች ድጋፍ
- ልጆች ትምህርት ቤት እንዲመዘገቡ ጥቆማ
- ልጆች ትምህርት ቤት ሲሄዱ እንዳስፈላጊነቱ አብሮ መሄድና ግንኙነት መቀጠል

3. ወጣቶች
እስራኤል ውስጥ ወላጅ ለሌላቸው ወጣቶች አፓርታማ ማስተዳደርና የገንዘብ ድጋፍ መስጠት። መኖሪያ ቤት ለማግኘት ማፈላለግ። ለጥናትና ለሥራ የሚሆኑ ሁኔታዎች ጋር ጥቆማ። የስነ አእምሮ ድጋፍ። በፈቃደኝነት የሚሠሩ ሠራተኞች አብሮ የመሆንና የመካሪነት/የአራያነት አገልግሎት እንዳስፈላጊነቱ ይሰጣሉ።

4. ማህበረሰቦች
የስደተኛ ማህበረሰቦችን እድገት የማገዝና አብሮ የመሆን
ለስደተኛ ማህበረሰብ መሪዎች የቅንጅት፣ የሕብረተሰብና የስነ አእምሮ አሠራሮች ማቅረብ

5. የድንገተኛ እርዳታ
ግለሰቦች ወይም ቤተሰቦች የሕክምና ወይም ሰብዓዊ አድጋ በሚያጋጥማቸው ጊዜ ድንገተኛ እርዳታ መስጠት።

6. መብቶች ማበረታታት
የጥገኝነት ፈላጊዎችንና የስደተኞችን ማህበራዊ መብቶች ለማሻሻል ከባለሥልጣኖች ጋር አብሮ የድጋፍ ሥራ መሥራት
የጥገኝነት ፈላጊዎችንና የስደተኞችን የመከላከል መብት ከሕግና ከውሳኔ ሰጭ አካል ባለሥልጣኖች ጋር የመገፋፋት

በይበልጥ መረጃ ለማግኘትና ከዚህ በላይ ስለተጠቀሱት ይበልጥ እርዳታ ለማግኘት፣ እባክዎን የሚከተለውን ይገናኙ፦

Assaf - The Organization for Psychological Aid to Refugees and Asylum Seekers (ለስደተኞችና ጥገኝነት ፈላጊዎች የስነ አእምሮ እርዳታ ድርጅት)
52 Golomb St. 2nd floor (2ኛ ፎቅ), Tel Aviv (አዲሱ የአውቶቡስ ፌርማታ ማዕከል አጠገብ)።
ስልክ ቁጥር፦ 07-22513838 ፣ ፋክስ ቁጥር፦ 07-22513837፣
ኢሜል፦assafaid@gmail.com | ድህረገጽ፦ www.assaf.org.il

Mesila
Assistance and Information
Center for Foreign Workers

Municipality of Tel Aviv - Jaffa
Social Services Administration
Social Services Division - South

# ለጥገኝነት ፈላጊዎችና ለስደተኞች መረጃና ሰብዓዊ እርዳታ

Mesila — ለውጭ አገር ሠራተኞች እርዳታና የመረጃ ማዕከል - በቴል አቪብ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ሥር የሚተዳደር ሲሆን ይህ ከተማ ነዋሪዎቹ መንግሥቱ ስለነሱ ያለው አመራር የተለየ ቢሆንም ባይሆንም ደህንነታቸውን መጠበቅ የሚፈልግ ድርጅት ነው።

አድራሻ፦ 3 Rishon Lezion St., Tel Aviv
ስልክ ቁጥሮች፦ 03-6879727 / 03-6877796
የመቀበያ ሰዓት፦ ሰኞ 12:00 — 18:00
ረቡዕ 14:00 — 19:00

## ጥገኝነት ፈላጊዎችን ለመርዳት Mesila የሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች

1. በተለያዩ መስኮች የግል እርዳታ (ሰብዓዊ፣ ሲቪል አስተዳደራዊ፣ ሕጋዊ)
2. በስደተኛ ማህበረሰቡና በተለያዩ ተቋሞችና ባለስልጣኖች መካከል ሽምገላ (ደህንነት፣ ጤና፣ ትምህርት)

3. አቋምና ቪዛ በሚፈለግበት ጊዜ እርዳታና አመራር
4. የቤት ውስጥ ጥቃት በሚደርስበት ጊዜ መድረስ
5. ችግር ላይ ያሉ ልጆችንና ልዩ እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ልጆች ማግኘትና መንከባከብ
6. ልጆችን መዋለ ሕጻናትና ትምህርት ቤት የማስመዝገብ እርዳታ
7. ለልጆች የግል አስተማሪ
8. ለልጆች የመዝናኛ ቀኖችና እንቅስቃሴዎች
9. ጠባቂ ለሌላቸው ልጆች እንክብካቤ፥ የግል መካሪ፣ ከሃፖኤል ቴል አቪብ ጋር በመተባበር የእግር ኳስ ቡድን፣ ከቤት አልባ መጠለያ የተለየ የመኖሪያ ሁኔታ መፈለግ
10. ለአዋቂዎች የእብራይስጥ ኡልፓን ትምህርት፥ ለጀማሪዎች፣ መሃከለኛና ከፍተኛ
11. ለአዋቂዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት፥ ለጀማሪዎች፣ መሃከለኛና ከፍተኛ ማታ ማታ የሚሰጡ ክፍሎች
12. የጤና ችግሮችን በተመለከተ እርዳታና መረጃ፥ በሽታ ስለመከላከልና ስለ ሕክምና ምክር፣ ሴቶች ከወለዱ በኋላ እርዳታ፣ በ Meuchedet HMO በኩል ልጆችን የጤና ዋስትና ስለማስመዝገብ
13. Mesila አጠገብ ከሚገኘው የእናትና የልጅ ክሊኒክ ጋር በቅርብ አብሮ በመሥራት ዕድሜያቸው ከስድስት ዓመት በታች ለሆኑ ልጆች አገልግሎት መስጠት
14. ለጥገኝነት ፈላጊ ልጆች ከትምህርት ቤት በኋላ መሳተፊያ ቡድኖች ማቋቋም
15. ልቤት አልባ መጠለያዎች ውስጥ የእንቅስቃሴ እርዳታ
16. ኦፊሲዬላዊ ቅጾችን ለመሙላት እርዳታና ምክር
17. የአመራር ድጋፍ መፈለግ - ከመንግስት ጋር፣ ከክኔሴት ኮሚቴዎች ጋር፣ የማዘጋጃ ቤት ክፍሎች ጋርና ከሌሎች ባለስልጣኖች ጋር ግንኙነት በመፍጠር

<u>የጥገኝነት ፈላጊዎች ልጆች የትምህርት መብቶች፥</u>

ዕድሜያቸው ከ3 ዓመት እስከ 16 ዓመት ያሉ ልጆች ሁሉ የከተማው ትምህርት ቤቶች ውስጥ የመማር መብት አላቸው፣ መዋለ ሕጻናትንና ከፍተኛ ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ። ይህንን መብት ለማስፈጸም Mesila በደስታ እርስዎንና ልጆችዎን ይረዳዎታል።

Mesila - ሜሲላ
ለውጭ አገር ሠራተኞች እርዳታና የመረጃ ማዕከል
የቴል አቪብ - ጃፋ ማዘጋጃ ቤት
የማህበራዊ አገልግሎቶች አስተዳደር
የማህበራዊ አገልግሎቶች ደቡብ ቅርንጫፍ

רופאים לזכויות אדם - ישראל (ע"ר)
أطباء لحقوق الانسان-إسرائيل
Physicians For Human Rights - Israel

# በጤናና ሕክምና መስክ ውስጥ የጥገኝነት ፈላጊዎችና የስደተኞች መብትና መረጃ

ሁሉም ሰው አጥጋቢ የጤና አገልግሎቶች የማግኘት መደበኛ መብት አለው። PHR-Israel ጥገኝነት ፈላጊዎችና ስደተኞች የጤና መብታቸውን እንዲያገኙ ከመንግሥት ተቋማት፣ ከዋስትና ድርጅቶች፣ ከቀጣሪዎችና ከሌሎች ጋር አብሮ ይሠራል። ድርጅቱ ብሔራዊ ዋስትና የሚሰጠው ዋስትና በእስራኤል ለሚኖሩ ጥገኝነት ፈላጊዎችና ለስደተኞችም እንዲሠራ መፍትሔ ለማግኘት ይጣጣራል።

<u>እስራኤል አገር የሚኖሩ ስደተኞችና ጥገኝነት ፈላጊዎች የተለያዩ መብቶ አሏቸው። መብቶችዎ እንዲጠበቁ መወትወት አለብዎት፣ መብቶችዎ ምን እንደሆኑ ማወቅዎም አስፈላጊ ነው፦</u>

- ቀጣሪዎ ያዘጋጀው የግል የጤና ዋስትና ማግኘት።
- ሥራ ላይ አደጋ ቢደርስ ወይም በእርግዝናና በወሊድ ጊዜ የሚረዳ ዋስትና በብሔራዊ ዋስትና በኩል ማግኘት።
- እስራኤል ውስጥ የሚገኙ ሆስፒታሎች ሁሉ ጋር ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ የሚሰጥ የድንገተኛ ሕክምና።
- የእናትና የልጅ ክሊኒኮች ውስጥ በእርግዝናና በወሊድ ጊዜ የሚሰጡ የመቆጣጠሪያ አገልግሎቶች።
- ለልጆችዎ የጤና ዋስትና።
- ሥራ ከሌልዎት የጤና ዋስትና በግልዎ መግዛት ይችላሉ።

መብቶችዎን ስለማስጠበቅ፣ በይበልጥ ዝርዝር መረጃ ለማግኘትና ጤናን በተመለከተ ባለስልጣኖችን ስለመገናኘት እርዳታ ከፈለጉ፣ እንዲሁም ሕጋዊ ትብብር ካስፈለግዎት PHR-Israel እንድትገናኙት ይጋብዛችኋል። ስልክ ቁጥር፦ 03-5133103, 03-5133104.

## በተጨማሪም PHR-Israel በፈቃደኝነት የሚሠሩ ዶክተሮች ያሉበት ክሊኒክ አለው። ክሊኒኩ እስራኤል የሚኖሩ የጤና ዋስትና ለሌላቸው ሰዎች ሁሉ አገልግሎት ይሰጣል።

<u>የክሊኒኩ የሥራ ሰዓት፦</u>
እሁድ፣ ማክሰኞ፣ ረቡዕ፦ ከ 17:00 ሰዓት እስከ 20:00 ሰዓት (ቀጠሮ መያዝ አያስፈልግም)
ሰኞ፣ የማህጸን ሐኪም፦ ከ 17:00 ሰዓት እስከ 20:00 ሰዓት (እባክዎን አስቀድመው ቀጠሮ ይያዙ)
አርብ፦ የልጆች ክሊኒክ ከ 9:00 ሰዓት እስከ 12:00 ሰዓት

<u>የክሊኒኩ አድራሻ፦</u>
9 Dror St., Tel Aviv — Jaffa
ክሊኒኩን በቀጥታ በስልክ መገናኘት ይቻላል፦ 03-5133120

# እስራኤል ውስጥ ለጥገኝነት ፈላጊዎች እርዳታ የሚሰጡ ድርጅቶችና ስልክ ቁጥራቸው፦

የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽነር (United Nations High Commissioner for Refugees)
ስልክ ቁጥር፦ 03-5167700

በቴል አቪቭ ዩኒቨርሲቲ የስደተኞች መብት ፕሮግራም (Refugee Right Program at Tel Aviv University)
ስልክ ቁጥር፦ 03-6406772 / 03-6405264

ስደተኛ ሠራተኞች የመረጃ መስመር (Hotline for Migrant Workers)
ስልክ ቁጥር፦ 03-5602530

ካቭ ላኦቬድ (Kav Laoved)
ስልክ ቁጥር፦ 03-6883766

የአፍሪካ ስደተኞች እድገት ማዕከል (A.R.D.C.—African Refugees Development Center)
ስልክ ቁጥር፦ 054-6388633 (እንግሊዝኛና ፈረንሳይኛ) / 054-6816333 (እንግሊዝኛና አማርኛ)

ለስደተኞችና ጥገኝነት ፈላጊዎች የስነ አእምሮ እርዳታ ድርጅት (A.SS.A.F. — Organization for Psychological Aid to Refugees and Asylum Seekers)
ስልክ ቁጥር፦ 07-22513838

ለውጭ አገር ሠራተኞች እርዳታና የመረጃ ማዕከል (Mesila - Assistance and Information Center for Foreign Workers)
ስልክ ቁጥር፦ 03-6879727 / 03-6877796

ለሰብዓዊ መብት የቆሙ ዶክተሮች (PHR — Physicians for Human Rights)
ስልክ ቁጥር፦ 03-5133120

ይህ ሕትመት የተዘጋጀው በስደተኛ ሠራተኞች የመረጃ መስመር ሲሆን፣ ለሕትመቱ የገንዘብ ድጋፍ የሰጠው የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽነር ነው።